
# በደቡብ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት

# በየም ልዩ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት

**በዘላቂ መሬት አያያዝ ፕሮጀክት /SLMP/ የበጀት ድጋፍ እና በማህበረሰቡ ተሳትፎ በሾሸርና አልማማ ቀበሌ በአልማማ ሸን- ንዑስ ተፋሰስ ዉስጥ በተሰራዉ ጤረጳዛማ እርከን በመጣዉ ለዉጥና ዉጤታማነት ዙሪያ የተቀመረ ምርጥ ተሞክሮ ዶክመንት**




**2015 ዓ/ም**

ማዉጫ ገፅ


1. መግቢያ ...1
2. የተሞክሮዉ ዓላማ...4
3. የተሞክሮዉ ግብ ...4
4. የፕሮጀክቱ እንቅስቃሴ ...5
5. የፕሮጀክቱ ዉጤት(Out comes) ...5
6. ዘርፈ ብዙ ጠቀመታዉና ዘለቀታዉ ...7

6.1 ከኢኮኖሚያዊ ተቀመታዉ አንጻር...7

6.2 ከማህበራዊ ተቀመታዉ አንጻር...7

6.3 ከአከባቢያዊ ተቀመታዉና ዘለቀታዉ አንጻር...7

7. ተከኖሎጅዉን ማስፋፋት (Replicability)...7
8. መደምደምያና አስተያየት (Conclusion and Recommendation) ...7

8.1 መደምደምያ(Conclusion)...7-8

8.2. አስተያየት(Recommendation)...8-9

መግቢያ፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ እየተገበረች ያለችሁ «በአየር ንብረት ለዉጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ»ግስጋሴ ዉስጥ የተፈጥሮ ሀብቶችን በመጠበቅ፣ በማንከባከብና ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ብልፅግና ጉልዕ ሚና እንድኖረዉ ለማድረግ በመሬት አያያዝና አጠቃቀም ላይ መሠረት ያደረገ ልማት መተግበር አስፈላጊ ከመሆኑም አልፎ ወሳኝ ሆኖ ተገኝተዋል ፡፡አስፈላጊና ወሳኝ የሆነበትም ምክንያት የአየር ንብረት ለዉጡን እየተቋቋመ ምርት የማይሰጡ መሬቶች ምርት እንድሰጡ ማድረግ/ምርት ማሳደግና ጎርፍን በመከላከል የገፀና የከርሰ ምድርን ዉሃ በማበልፀግ የመስኖ ዉሃ አማራጭ መፍጠር የሚያስችል በመሆኑ ነዉ፡፡ ከዚህ በመነሳት በአሞ ናዳ ወረዳ ከ 2006 ዓ/ም ጀምሮ በዘላቂ መሬት አያያዝ ፕሮጀክት/SLMP/ እና በህብረተሰቡ ተሳትፎ በግቤ ተፋሰስ ዉስጥ ያሉ ስድስት ቀበሌዎች ማለትም በከርዋ፣ በጎሩምና ሀንገሪ፣ በመላካ፣ በሼሞና መተሎ፣ በሾሸር አልማማና በከርዝደዮ ቀበሌዎች ከላይ ከተገለፅዉ ሐሳብ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉ ሰፊ ሥራዎች ተሰርቶ አመርቂ ለዉጦችን ለማየት ተችለዋል፡፡

ከዚህ መነሻ ይህ ተሞክሮ በደቡብ ክልል በየም ልዩ ወረዳ በሾሸር አልማማ ቀበሌ ዉስጥ የሚገኝ ሲሆን ከወረዳዉ ዋና ከተማ ሣጃ 34 ኪሎ ሜትር ላይ ስገኝ የተፋሰሱ ስፋት 637.14 ሄ/ር ሆኖ ከባህር ወለል በላይ ከ2939 እስከ 1630 ሜትር አማካይ የዝናብ መጠን ደጋማ አግሮኢኮሎጅ ክልል ዉስጥ ይካተታል፡፡ ይህን አከባቢ ለየት የሚያደርገዉና ተሞክሮ እንቀመር ግድ የሆነበት ምክንያት በጣም ተራራማ ፣ ወጣገባና ተዳፋታማነቱ ከ30% በላይ በሆነዉ ቦታ ላይ በተሰራዉ ጤረጰዛማ እርከን ሥራ ኢኮሎጅካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ሁለንትናዊ ጠቀመታ ያላቸዉ ሥራዎች በመሠራታቸዉ ዘመናዊ የእንስሳት መኖ ፣ ተጨማሪ የእርሻ መሬትና የሰብል ምርት፣የመስኖ ዉሃ አማራጭ ለማግኘት በመቻሉ ነዉ፡፡

በዚህ ንዑስ ዉስጥ የሚገኙ አጠቃላይ ሕዝብ ብዛት ወንድ 457 ሴት 468 ድምር 925 ፤የተፋሰሱ ተጠቃሚ ማህበረሰብ ብዛት ወንድ 321 ሴት 211 ድምር 531፡፡ማህበረሰቡ ጠንካራ የተፋሰስ ተጠቃሚ ማህበር በማደራጀት እና በማህበራት መተዳደሪያ ደንብና መመሪያ መሠረት ተደራጅቶ በማልማት እየተጠቀሙ ይገኛሉ፡፡የአከባቢዉ ማህበረሰብ ዋነኛዉ መተዳደሪያ በእርሻ ሥራ ሲሆን የሚመረቱ ዋና

ዋና ሰብሎች፡ስንዴ፣ ገብስ፣ ምስር፣ እንሰት፣እና ፍራፍሬ(አፕል)ናቸዉ፡፡ ህብረተሰቡ አዳድስ ተክኖሎጅዎችን የመቀበልና ተደራጅቶ በጋራ የመስራት ልምድ ያላቸዉ ናቸዉ፡፡ በዚህ ቀበሌ ዉስጥ የተሰራዉ ሥራ ለወደፊት እንደ ቱሪስት መስዕብነት የሚያገለግል ተፈጥሯዊ ልዩ ዉብ መልካዓ ምድርም ጭምር አለዉ፡፡በለላ በኩል በለማዉ ጨረጰዛማ እርከን ጠርዝ ላይ የተተከለዉ ዘመናዊ የእንስሳት መኖ በስፋት እየለማ እንዳለና ህ/ሰቡ ከእርባታዉ ዘርፍ ከዝህን በፊት ያልነበረ ወይም ያልተለመደ ጥቅም እያገኙ ይገኛሉ፡፡ በሌላ አነጋገር አርሶ አደሩ የራሱን ማሳ በተገቢዉ ባለማንከባከቡም መሬቱ በየዓመቱ ስለምታረስ የመሬት ለምነት መቀነስ፣ በጎርፍ መታጠብ፣ሥነ አካላዊና ሥነ ሕይወታዊ የአፈርና ዉሃ ጥበቃ ሥራዎችን በአግባቡ ያለመሰራትና ያለማንከባከብ ፣የአፈር አስዳማነትና የምርትና ምርታማነት ከዓመት ወደዓመት እቀነሰ መምጣት፣ የእዕል ዋጋ መጨመርና የኑሮ ዉድነት እየተስተዋለ ይገኛል፡፡( በተለየ መልኩ በአካባቢው ገጠመውን ችግር ግልጽ ተገርጎ ቢጻፍ ለምሳሌ ናዳ ፤ በጎርፍ የመኖ እጠረት...) ለእነዝህ ችግሮች የመጀመሪያዉ መፍተሔ ከላይ እንደ ምክንያት የተገለጹትን በትክክል በመተግበርና በገቢያ መሪ ሰብሎች ላይ ትኩት በማድረግ ምርትና ምርታማነትን የሚጨምሩ ተክኖሎጅዎችን አሟልቶ መጠቀም ነዉ፡፡ለላኛዉ መፍተሔ በተከለለዉ ንዑስ ተፋሰስ ዉስጥ ከመሬቱ አቀማመጥ፣ ከማልማት አቅምና ተዳፋታማነቱ ጋር የሚስማሙ ሥነ አካላዊና ሥነ ሕይወታዊ የአፈርና ዉሃ ጥበቃ ተክኖሎጅዎችን ለይቶ መስራትና ከአከባቢዉ ሥነምህዳር ጋር ተስማሚ የሰብል ዝርያዎችን መርጦ በመዝራት ምርት የማይሰጠዉን መሬት ምርት እንድሰጥ ማድረግ ነዉ፡፡ ለዝህም **ጨረጰዛማ እርከን** ሥራ እንደጥሩ አማራጭ ተደርጎ ተወስደዋል፡፡

ጠረጼዛማ እርከን ከመሠራቱ በፊት



ጠረጼዛማ እርከን ከተሠራ በኋላ



ይህን ንዑስ ተፋሰስ ለየት የሚያደርገዉ የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት ፕርንስፐሎችን ያሟላና በተግባር ማየት የተቻለበት በመሆኑ ነዉ ፡፡ይኼዉም

1. በተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃዉ ዘርፍ፡የጠረጰዛማ እርከን ሥራ፣ ዉሃ ማሰባሰብ ሥራ፣የደን ጥምርእርሻ ሥራ፣ የአፈር ለምነት ማሻሻያ ሥራዎች፣
2. በሰብል ልማትና ጥበቃዉ ዘርፍ፡ የጨረጰዛማ እርከን ተሠርቶ በተገኘዉ መሬት ላይ ከአከባቢዉ ሥምህዳር ጋር ተስማሚ የሰብል ዝሪያዎችን (ገብስ፣ስንዴ፣ ምስር፣የደጋ ፍራፍሬዎችን) በመለየትና በማልማት ዉጠታማ ሆኖ መታየቱ፣



3. በእንስሳት ሀብት ልማቱ ዘርፍ፡ በተሠራዉ ጨረጰዛማ እርከን ጠርዝ ላይ በሙሉ መኖ ሣር በመትከል መኖ ልማትና የግንጣይ(ችግኝ) ማባዛት ሥራ፣ከልቅ ግጦሽ ወደ አጭዶ የመመገብ ዘዴ መሻገር(ለድለባና ማሞከት፣ ወተት ልማት)፣ንብ ማነብ ሥራ ፣ወዘተ ዕድሎች ተፈጥረዋል፡፡ በተለይ ከመኖ ልማት አንጻር እንደ ችግኝ ማባዣ ጣቢያ በመጠቀምና 300 ሜ3 ለሌሎች አጎራባች ቀበሌዎችና ተፋሰሶች በማሰራጨት በገንዘብ ስተመን 105,000.00 ብር ያህል ለግንጣይ ግዥ የሚወጣዉን ገንዘብ ማትረፍ ተችለዋል፤ በሌላ በኩል ታጭዶ የተሸጠ 12000 ብር፣ በድምሩ 117000.00 ብር የሚገመት ገቢ ተገኝተዋል፡፡ከድለባ አንጻር አንድ ወጣት በሬ ደልቦ እስከ 30000 ብር ሸጠዋል፡፡ ባጠቃላይ ሥራዉ ከተጀመረበት ጊዜ እስካሁን ያለዉን ስንመለከት

አሁን ያለዉም ይሁን ለቀጣይ ተዉልድ ዘላቂና ( ማህበራዊና- ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያለዉ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

2. የተሞክሮዉ ዓላማ ፤

- አ/አደሩ ይህን ተሞክሮ በመዉሰድ የግል ማሳዉን በዝህ ልክ አልምቶና አንከባክቦ እንድጠቀም ለማስገንዘብ፣
- የወረዳችን መሬት አቀማመጥ በአብዛኛዉ ተራራማ፣ ተዳፋታማ እና ለልቅ ግጦሽና ጎርፍ የተጋለጠ በመሆኑ በጤረጰዛማ እርከን ሥራ በመቀየር ተፈጥሮን እየጠበቅን ምርት ማምረት እንደምቻል ለማስተማር፣
- የሥራዉን ዉጠታማነት ለወረዳዉ ማ/ሰብ ከማስገንዘብ አልፎ እንደ ክልልና ሀገር ዕዉቅና እንድያገኝ ለማድረግ ነዉ፡፡

3. የተሞክሮዉ ግብ ፤

- በወረዳችን ገጠር ቀበሌዎች ዉስጥ ያሉ መሬቶች በተፈጥሮዉ ተራራማ፣ ተዳፋታማ እና በጎረፍ የተጋለጡትን ቦታዎች በጤረጰዛማ እርከን ሥራ በመሸፈን የጎርፍ አደጋ ቀንሶና ወደ ምርት ማምረት ደረጃ ደርሶ ማየት
- በጠረጰዛማ እርከን የለማዉ መሬት ለምነቱ ተሻሽሎ ፣ የዕፅዋትና ብዛሐሕይወት ጥበቃና በኢኮኖሚዉ ዘርፍ

  ከአከባቢዉ ሥነ ምዕዳር ጋር ተስማሚ የሰብልና እንስሳት ልማት ሥራዎች ለምቶ የማ/ሰቡ ኑሮ ተሸሽሎ ማየት ፤

  - ይህ ተከኖሎጅ ባልተስፋፋባቸዉ አከባቢዎች ተስፋፍቶና ዉጤታማ ሆኖ የመሬት አያያዝ ግንዛቤና የሀገር ኢኮኖሚ ጨምሮ ማየት፡፡

  4. የፕሮጀክቱ እንቅስቃሴ፤

  ይህ አልማማ ሸን ንዑስ ተፋሰስ በዘላቂ መሬት አያያዝ ፕሮጀክት ከሚደገፉ ንዑስ ተፋሰሶች አንዱ ስሆን በ2008 ዓ/ም ጀምሮ በተፋሰሱ ዉስጥ ያሉትን ህ/ሰብ ክፍሎችንና

ባለድርሻ አካላትን በማወያየትና በመተማመን አሳታፍ ዕቅድ በማዘጋጀት የፕሮጀክቱንና የህብረተሰቡን አስተዋፅኦ በመለየት ወደ ትግበራ ተገብተዋል፡፡ወደ ትግበራ ምዕራፍ ስገባ ለሥራዉ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በማሟላት ማለትም የሥራ ጉልበት ፣የሥራ መሳሪያ(ተክኖሎጅዎችን)፣የእርሻ ግብዓቶችን፣በማዘጋጀት ሥራዉ ተጀምረዋል፡፡ ሥራዉ የጤረጰዛማ እርከን አቀያየስና አቆፋፈር ሳይንስን ተከትሎ ተፈፃሚ በማድረግ ሥነ አካላዊ ሥራዉ ተሰርቶ ስያበቃ ከዚህ በፊት ሰብል የማይመረትበት ነገር ግን በተፈጠረዉ መሬት ከአከባቢዉ ሥነምህዳር ጋር ተስማሚ እና ኢኮኖሚካሊ አዋጭ የሆኑ የሰብል ዝሪያዎችን የመዝራትና ጠርዝ ጠርዙን በዘመናዊ መኖ ሳር የመሸፈን እንድሁም ለደን ጥምር እርሻ የሚመረጡ የዛፍ ችግኞችን የማስተከል ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡

5. የፕሮጀክቱ ዉጤት(Out Comes)

ይህ አልማማ ሸን ተፋሰስ ተለይቶ የጥናትና ድዛይን ሥራ ተሰርቶ በተከናወኑ ተግባራት የመጣዉ ለዉጥና ዉጤት እንደሚከተለዉ በዝርዝር ይገለፃል፤

- ❖ ከተፋሰሱ (268.665 ሄ/ር መሬት) በጤረጰዛማ እርከን ሥራ በመልማቱ የጎርፍና የናዳ ጉዳት ቀንሰዋል፣
- ❖ የተከለለዉ ተፋሰስ ለዘመናት ልቅ ግጦሽ በማሰማራት የሚታወቅ ሲሆን ጤረጰዛማ እርከን ከተሰራ ቡኋላ በዘመናዊ ዘዴ ተክሎና አጭዶ የመመገብ ሥርዓት ተፈጥሯል፣
- ❖ ለእርሻ ሥራ የማይታሰብ ተራራማ መሬት ጤረጰዛማ እርከን በመሰራቱ ተጨማሪ የእርሻ መሬት፣ ተጨማሪ ምርትና የሥራ እድል እንድፈጠር አድርጓል፣
- ❖ ለአብነት የሚጠቀሱ የሥራዉ ዉጤቶች፡
    - ➢ በ2013 ዓ/ም 11.13 ሄ/ር መሬት በገብስ ሰብል በመሸፈን 329.5 ኩ/ል ምርት ተገኝተዋል፤ በገንዘብ ስተመን 948,960.00 ብር ነው፡፡

- በዘመናዊ እንስሳት መኖ ሣር 162 ሄ/ር የተሸፈነ ሲሆን ለድለባ፣ ወተት ምርትና እንደ መኖ ማባዣ ጣቢያነት እያገለገለ በተጨማሪም አጭዶ ለመመገብ  በዓመት ሦስት ዙር እስከ 12000 ብር በመሸጥ የገቢ ምንጭ እየሆነ ይገኛል፡፡



በጠረጼዛማ እርከን መኖ ልማት



የበግ እርባታ

❖ ከአከባቢዉ እየጠፉ የሄዱ የነበሩ የተለያዩ የዕፅዋት ዝሪያዎችና ብዛሕይወት እየተመለሰ መሆኑን በመጣዉ ለዉጥ ለማረጋገጥ ተችለዋል፡፡ (የ ዕጽዋት አይነት ቢዘረዘሩ )

❖ ቁልቁለቱን ተጠቅሞ እየተወረወረ የሚወርደዉ የጎርፍ ዉሃን መቆጣጠር በመቻሉ የመሬት ናዳ፣ የአፈር ክለት/መሰሸርሸር ቀንሰዋል፤ የከርሰ-ምድርና የገፀ-ምድር ዉሃ በልፅጓል፤ከዚህ የተነሳ የመስኖ ዉሃ አማራጭ መፍጠር በሚቻልበት ደረጃ ደርሰዋል፡፡

6. ዘርፈ ብዙ ጠቀመታዉና ዘለቀታዉ አንጻር ፤

6.1 ከኢኮኖሚያዊ ተቀመታ አንጻር፡ ይህ በጤረጰዛማ እርከን ሥራ ፍዝካል አቀማመጡ የተቀየረዉ መሬት በዘላቂነት ምርት እንደምሰጥና ለሕ/ሰቡ የሚሰጠዉ ጥቅም የማይቋረጥና ለትዉልድ የሚሸጋገር እንደሆነ፣

6.2 ከማህበራዊ ጠቀመታ አንጻር፡ የአብሮነትና የጋራ ሀብቶችን በጋራ የመጠበቅ፣ የማንከባከብ፣ እኩል ተጠቃሚ የመሆንና አብሮ ሠርቶ አብሮ ማደግን ራዕይ ያነገበ እንደሆነ፣

6.3 ከአከባቢያዊ ጠቀመታና ዘለቀታ አንጻር፡ በመሬት ላይ የሚደርሱ ሰዉ ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋዎችን የመከላከል፣የብዛሐ ሕይወት ጥበቃ፣ የአየር ንብረት ለዉጥን ተፅዕኖ መቋቋምና መቀነስን ዓላማ ያደረገ እንደሆነ የሚያመላከት ነዉ፡፡

7 የተክኖሎጅዉ መስፋፋት (Replicability)

ይህ ጤረጰዛማ እርከን ሥራ አነስተኛ ወጪን የሚጠይቁ የቅየሳ ተክኖሎጅዎችንና በተግባር የተረጋገጡ የፈጠራ ስልቶችን በመጠቀም የሚሠራ ሲሆን እንደ ሀግርም ይሁን እንደ ወረዳችን ምንም ዓይነት ኢኮኖሚያዊ ጠቀመታ የማይሰጡ ታራራማና ተዳፋታማ መሬቶችን ፍዝካል አቀማመጣቸዉን በመቀየር ወደ ምርት ማምረት ደረጃ ማድረስ የሚቻል በመሆኑ ይህን ተሞክሮ በመዉሰድ ወደ ሁሉም ማስፋፋት የሚቻል ነዉ፡፡

8 . መደምደሚያ እና አስተያየት(Conclusion and Recommendation)

8.1 መደምደሚያ (Conclusion)

ከላይ በመግቢያዉ እንደተገለፀዉ የአልማማ ሸን ንዑስ ተፋሰስ በየም አልማማ ቀበሌ ዉስጥ የሚገኝ ሲሆን የጥናትና ድዛይን ሥራ ተሰርቶ ወደ ትግበራ ከተገባበት ከ 2006 ዓ/ም ጀምሮ በተከለለዉ 268.665 ሄ/ር ዉስጥ በሙሉ የጤረጰዛማ ቅየሳና ቁፋሮ ሥራ ተከናዉነዋል ፡፡ የተሰራዉ ሥራ ዘርፈ ብዙ የሆነ ኢኮኖመያዊ ፣ ማህራዊና አከባቢያዊ ጠቀመታዎችን ያስገኘ እንደሆነ አጭር ባጭሩ ለማብራራት ተሞክሯል፡፡ስለሆነም አሁን ባለዉ ተጨባጭ ሁኔታ የፊዝካል ሥራዉ ተጠናቅቆ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማስገኘት ምችልበት ደረጃ ላይ እየደረሰ ስለሆነ የሚከናወኑ ማንኛዉም የልማት እንቅስቃሰዎች የተሰሩ ስትራክቸሮችን ዘላቅነትና በጥገናም ጭምር እየተጠበቀ ዉብና ማራኪ የሚያደርጉ ተግባራት መከናወን ይኖርባቸዋል፡፡ ይኼዉም ዘርፈ ብዙ ጠቀመታ ያላቸዉ የደን ዛፍ ዝሪያዎችን መትከልና ማንከባከብ፣የአፈሩን ለምነት የሚያሻሽሉ ሥራዎችን ማለትም ኮንፖስት ፣ አረንጓዴ ማዳበሪያ ፣ፊግና የመሳሰሉትን መጠቀምና የአፈር አስዳማነትን ለመከላከል አፈር ማስመርመርና መቆጣጠር ፣ገቢያ መሪና አዋጪ የሰብል ዝሪያዎችን ለይቶ ማልማት..ወዘተ ፡፡ለዚህ ሁሉ ኃላፊነቱን የቀበሌዉ ማ/ሰብና የን/ተፋሰሱ ህ/ሰብ አሁን እያደረገ ካለዉ በላይ መጠበቅና ማንከባከብ ይኖርባቸዋል፡፡

8.2 አስተያየት (Rcommendation)

ይህ የአልማማ ሸን ንዑስ ተፋሰስ ቀደም ሲል ከነበረበት የመሬት አቀማመጥ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ማህበራዊ፣ አከባቢያዊ ገፅታዉና ሁኔታ እና አሁን የደረሰበትን ስንመለከት የተለየ ስዕል ያሳየበት ዋነኛዉ ምክንያት ፡

- አዳድስ ተከኖሎጅዎችን በዕዉቀት በመታገስ ወደ መሬት ማሳረፍ በመቻሉ፣
- መንግስትና ህ/ሰቡ ተስማምቶና ተደጋግፎ በመስራታቸዉ፣
- በሐሳብ ይለወቅ በተግባር የሚያምን ህ/ሰብ በመፈጠሩ ነዉ፡፡

ስለሆነም በዚህ ንዑስ ተፋሰስ ተሠሮቶ ዉጤታማ የሆነዉ የጤረጸዛማ እርከን ሥራ ወደ ሁሉም አከባቢዎች ማለትም የዝህን ዓይነት የመሬት አቀማመጥ ባለባቸዉም ይሁን ከፍተኛ ተዳፋታማነት ወዳለባቸዉ ማስፋፋትና ዉጤታማነቱን መረጋገጥ ይነኖርበታል፡፡ በለላ አነጋገር ይህ ንዑስ ተፋሰስ አሁን ያለበት የመልማት ደረጃ የመጨረሻዉ ሳይሆን የለዉጥ መጀመሪያዉ ስለሆነ ገና ብዙ የተቀናጀ ሥራ መስራትን ይጠይቃል፡፡የተቀናጀ ሲባል የአከባቢዉን የተፈጥሮ ሚዛንና ብዛሐ ሕይወት መጠበቅ ሕ/ሰቡ የተቀበለበትና ያመነበት በፊዝካል ሥራ ጎርፍን መከላከልና ዉሃን ማበልፀግ የደን ጥምር እርሻ ልማት የአፈር ለምነት ችግሮችን ማሻሻል ሰብል ልማት መኖና እንስሳት ሀብት ልማት የአሰራር ዘዴዎች ጥራት(SMART) ዉጤታማነትና ምርታማነት መሪን የተከተለና አንዱ ለላዉን ሳይጎዳ ተደጋግፎ መልማት ይኖርበታል፡፡ በተለይ በምርት ማምረቱ ሂደት የተሰራዉን ስትራክቸር ቅርፅ በማይዛነፍ መልኩ ዉበቱ ተጠብቆ መታረስ ይኖርበታል፡፡ ይህ ተሞክሮ በዚህ ልክ እንድስፋፋ ስፈለግ በቀጣይ ትኩረት ልደረግ የሚገባዉ በተለይ ወደ ኢኮኖሚያዊ ጠቀመታዉ ሲሆን እንደ አከባቢዉ ተጨባጭ ሁኔታ አዋጭነት ያላቸዉና ገቢያ ተኮር የሆኑ ምርቶችን ለይቶ ማምረቱ እንደተበቀ ሆኖ ተሞክሮዉ እንድቀመር ያበቃዉ በፕሮጀክቱ በኩል የሚደረገዉ የድጋፍና የክትትል ሥርዓት ከቀበሌዉ ማ/ሰብና ባለድርሻ አካላት ጋር የተቀናጀና ጠንካራ ሥራ በመሰራቱ ስለሆነ የህ/ሰቡ ቁርጠኛ የሥራ ተነሳሽነትና የጋራ ሀብትን በጋራ አልምቶ የመጠቀም ባህል ወደፊትም ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

ጥቅል አስተያየት

ጥሩ  ስራ ነው  በተጨማሪ ተሞክሮው የተለየበት መመዘኛዎች በሰንጠረዥ ቢቀመጡ እነዲሁም ምርጥ ተሞክሮውን የቀመረውና ያዘጋጀው ሥም ስልክ ኢሜል መጠቀስ አለበት በጨረሻም ተጠቃሚ አርሶአደሮችን ሃሰብ  ቢጨመርበት ጥሩ ይሆናል፡፡

*ፎቶውን በተመለከተ

- ምርቱን ጭምር በሚያሳይ መልኩ በጨመርበት
- ተማሳሰይ ፎቶ ቢቀነስ
- የበግ እርባታው ወይም ድለባው መኖውን ሲመገብ በጋጣው አካባቢ አርሶአደሩን ጨምሮ የተነሳ ቢሆን ይመረጣል፡፡